# ሞጎተ ጥበብ አክሲዮን ማኅበር

# የተሻሻለ እና የተጠቃለለ

# የመመሥረቻ ጽሑፍ

አዲስ አበባ **2015** ዓ.ም

## የተሻሻለ እና የተጠቃለለ የመመሥረቻ ጽሑፍ

ይህ የተሻሻለ እና የተጠቃለለ የመመስርቻ ጽሑፍ የተዘጋጀው በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 በወጣው አዲሱ የንግድ ሕግ መሠረት ነው።

## አንቀጽ 1
## የማኅበሩ ስም

ማኅበሩ የተመዘገበው፣ ሥራውን የሚያከናውነውና ለNስተኛ ወገኞች የሚታወቀው እና የሚጠራው "ኖኅተ ጥበብ አክሲዮን ማህበር" በሚል ስም ነው።

## አንቀጽ 2
## የማኅበሩ አድራሻ

2.1. የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር አዲስ ነው።

2.2. ማኅበሩ እንደ አስፈላጊነቱ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል።

## አንቀጽ 3
## የባለአክሲዮኖች ስም፣ ዜግነት እና አድራሻ

የእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ስም፣ ዜግነት እና አድራሻ ከዚህ ሰነድ ጋር ሰንጠረዥ1 (አንድ) ተብሎ ተያይዟል።

## አንቀጽ 4
## የማህበሩ ዓላማዎች

ማኅበሩ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

4.1. መዋለ ሕፃናትን ማቋቋምና ማካሄድ

4.2. የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማቋቋምና ማካሄድ

4.3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችን (ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ) ማቋቋምና ማካሄድ

4.4. ልዩ ልዩ የምርምር፣ የሥልጠና እና ያማማከር አገልግሎቶችን ማካሄድ

4.5. የትምህርት መሳሪያዎችን ማምረት፣ ማስመጣትና ማከፋፈል

4.6. ከመደበኛ የመማር ማስተማር ሥራ ጎን ለጎን የአጭርና ረዥም የትምህርት ፕሮግራሞችን ወይም ስልጠናዎችን ማካሄድ፣

4.7. የሕትመት ስራዎችን ማከናወን

4.8. የመማርያ መጻሕፍትን ማዘጋጀት፣ ማተምና ማከፋፈል እና

4.9. የሪል ስቴት ሥራዎችን ማከናወን፣

4.10. የተማሪዎች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፣

4.11. በትምህርት ዘርፍ የፍራንቻይዝ አልግሎት ላይ መሣተፍ

ናቸው።

## አንቀጽ 5
## የአክሲዮን ካፒታል

5.1. የማኅበሩ የተፈረመው ዋና ገንዘብ ብር 152,406.000/ አንድ መቶ አምሳ ሁለት ሚሊየን አራት መቶ ስድስት ሺ.ህ/ ነው።

5.2. ከዚህ በላይ የተገለፀው ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 500 (አምስት መቶ) ዋጋ ባላቸው 304812 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሁለት/ በባለ አክሲዮኖች ስም የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው።

5.3. ከኢትዮ-ፓረንትስ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆች በጎ አድራጎት ማኅበር ተብሎ ከሚታወቀው ባለአክሲዮን በስተቀር ማናቸውም የማኅበሩ ባለአክሲዮን የሆነ ሰው ከማህበሩ የተፈቀደ ካፒታል ውስጥ እስከ 5% ዋጋ ካላቸው አክሲዮኖች በላይ በባለቤትነት መያዝ አይችልም።

5.4. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 5.3 የተደነገገው የአክሲዮን ብዛት ጣሪያ ቢኖርም በአክሲዮን ማኅበር መሥራች ባለአክሲዮኖችም ሆነ ሌላ የአክሲዮን ማኅበር አዲስ ገቢ ባለአክሲዮን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዓይነት መዋጮነት ለማኅበሩ ለማስገባት ፈቃደኛ ከሆነ ከማኅበሩ የተፈቀደ ካፒታል 10% ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖችን በባለቤትነት መያዝ ይችላል።

5.5. የሉሲ አካዳሚ አ.ማ 41,296 አክሲዮኖች ያሉት የአንዱ አክሲዮን ዋጋ ብር 500 (አምስት መቶ) በአጠቃላይ ብር 20,648,000 (ሃያ ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ) ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖች በሙሉ ኩኖጎተ ጥበብ አክሲዮን ማኅበር ጋር በቀድሞ የንግድ ሕግ ቁጥር 332 መሠረት የካቲት 2 ቀን 2013 በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር ቅ12/2724/4ለ/2014 ተመዝግቦ ተቀላቅሏል። ስለሆነም ማናቸውም የሉሲ አካዳሚ አክሲዮን ማኅበር መብትና ግዴታ ሰነዱ በኤጀንሲው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ወደ ኖጎተ ጥበብ አክሲዮን ማኅበር ተላልፏል።

5.6. የዚህ ማኅበር ባለአክሲዮን መሆን የሚችሉት ባለፉት ጊዜም ሆነ ወደፊት ልጆቻቸውን "በኢትዮ-ፓረንትስ ት/ቤት" የሚያስተምሩ ወላጆች እና ሌሎች የማኅበሩን አላማ ለማራመድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብሎ ቦርዱ የሚፈቅድላቸው የንግድ ተቋማትና ግለሰቦች ናቸው።

5.7. እያንዳንዱ ባለ አክሲዮን የያዘው የአክሲዮን ብዛት፣ የአንዱ አክሲዮን ዋጋና ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ አባሪ 2 (ሁለት) ሆኖ ተያይዟል።

## አንቀጽ 6
## የማኅበሩና የባለአክሲዮኖች የኃላፊነት ወሰን

6.1. ማኅበሩ ባለው ጠቅላላ ሀብት ለበለጠ ዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

6.2. ማንኛውም ባለአክሲዮን በያዛቸው አክሲዮች ዋጋ ለበለጠ ዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

## አንቀጽ 7
## ስለአክሲዮኖች

7.1. የማኅበሩ አክሲዮኖች በሙሉ በባለአክሲዮኖች ስም የተመዘገቡ ናቸው።

7.2. ባለአክሲዮኖች ለያዟቸው አክሲዮኖች የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሲሆን የምስክር ወረቀቱ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 273 በተመለከተው መሰረት የተዘጋጀ መሆን አለበት።

7.3. የማኅበሩ አክሲዮኖች በሙሉ መለያ ቁጥር የሚኖራቸው ሲሆን የመጀመሪያው ቁጥር 001 ሆኖ በተከታታይ ቁጥር ይሰጣቸዋል።

7.4. በንግድ ህጉ አንቀጽ 274 በተመለከተው መሠረት ተዘጋጅቶ የባለአክሲዮኖች መዝገብ በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ይቀመጣል።

7.5. አክሲዮኖች ሁሉ የማይከፋፈሉ ናቸው።

7.6. አክሲዮኖች በጋራ ባለሀብትነት የተያዙ በመያዣ ወይም በአላባ የተሰጡ ከሆነ በንግድ ሕግ አንቀጽ 270 እና 271 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 8
## አክሲዮኖችን ስለማስተላለፍ

8.1. አንድ ባለአክሲዮን የያዘውን አክሲዮን ከቤተሰቡ ውጭ ሌላ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ ወይም ለመሸጥ ሲፈለግ የማኀበሩ ባለአክሲዮች የግዥ ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል። በባለአክሲዮኖች መካከል አክሲዮኖችን ያለ አንዳች ገደብ ማስተላለፍ ይችላል።

8.2. ባለአክሲዮኖቹ በቅድሚያ መብታቸው ተጠቅመው ለሽያጭ የቀረበውን አክሲዮን ሽያጩ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ካልገዙት ማህበሩ ሊገዛው ይችላል። ከዚህ በላይ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ባለአክሲዮኖች ወይም ማህበሩ ካልገዙት ባለአክሲዮኑ አክሲዮኖቹን ለማንኛውም Nስተኛ ወገን የመሸጥ መብት አለው።

8.3. ባለአክሲዮኖች ወይም ማኀበሩ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 8.1 እና 8.2 በተገለጸው መሰረት አክሲዮን ሲገዙ፤አክሲዮን በሚገዙት በመጨረሻ ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይ በሚታየው የአክሲዮን ዋጋ ስሌት ነው። ሁለትና ከሁለት በላይ ገዢዎች ከቀረቡ ግን አክሲዮኑ በጨረታ ይሸጣል።

8.4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 8.2 መሠረት ማኀበሩ የሚገዛቸውን አክሲዮኖች በተቻለ መጠን ለአዲስ ወላጆች ለመሸጥ ጥረት ያደርጋል።

8.5. አንድ ባለአክሲዮን የቅድሚያ መብቱን በመጠቀም በሌላ ባለአክሲዮን ሊገዛ የሚችለው በዚህ የመመሥርቻ ጽሑፍ ንዑስ አንቀጽ 5.4 እና 5.5 የተመለከተው ከፍተኛ የአክሲዮን ቁጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ነው። ይህ ገደብ የኢትዮ-ፓረንትስ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆች በጎ አድራጎት ማህበር አይምለከትም።

8.6. በማኀበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 8.1 የተመለከተው ቢኖርም የአንድ ባለአክሲዮን ልጅ ትምህርቱን ጨርሶ ወይም በሌላ ምክንያት ከማኀበሩ ት/ቤት ቢወጣ፣ ባለአክሲዮኑ ፈቅዶ ካዛወረለት የማኀበሩ ባለአክሲዮን ሆኖ የመቀጠል መብት አለው።

8.7. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 8.1 እስከ 8.6 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም አክሲዮን ከአንድ ባለአክሲዮን ወደ ሌላ ባለአክሲዮን ወይም ወደ ሌላ Nስተኛ ወገን ለማስተላለፍ ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩ ለዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቀርቦ፣ በቃለ-ጉባዔ ይፀድቅና ቃለጉ-ባዔውም በስብሰባው ላይ በተገኙት የቦርድ አባላት እና ሽያጭ ሲሆን በሻጭና ገዥ፣ ስጦታ ሲሆን በስጦታ አድራጊው እና ተቀባይ ውርስ ሲሆን ደግሞ በውርስ ተቀባይ በፊርማ የተረጋገጠ ባለ አክሲዮን የመሆን ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

## አንቀጽ 9
## የትርፍ ክፍፍል

9.1. የትርፍ ድርሻ ለባለ አክሲዮኖች ከመከፈሉ በፊት ከተጣራው ትርፍ ላይ የሚከተሉት ወጪዎች ይቀነሳሉ።

9.1.1. በየሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ ከሚገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ 5% (አምስት በመቶ) እየቀነሰ በህግ ወደተወሰነው የመጠባበቂያ ገንዘብ መዛወር አለበት። ወደ መጠባበቂያው የተዛወረው ገንዘብ መጠን የማኀበሩ ዋና ገንዘብ አምስት በመቶ (5%) ላይ ሲደርስ የማዛወሩ ተግባር አስገዳጅነት ይቀራል።

9.1.2. በንግድ ሕግ አንቀጽ 433 በተገለፀው መሠረት በዲሬክተሮች ቦርድ አሳሳቢነት በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰኑ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች ከተጣራው ትርፍ ላይ እየተቀነሱ ሊያዙ ይችላሉ።

9.2. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቀናሾች ከተጣራው ትርፍ ላይ ከተነሱ በኋላ ቀሪው የተጣራ ትርፍ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ሆኖ ይከፈላል። የሂሳብ መግለጫዎችና የትርፍ ድርሻው በጠቅላላ ጉባኤው በፀደቀ በ3(Nስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ መከፈል አለበት።

9.3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 9.1 እና 9.2 የተገለፀው ቢኖርም የማኀበሩ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ የትርፍ ድርሻ እንዳይከፋፈልና ገንዘቡም ለማህበሩ ዓላማ ማስፈፀሚያ እንዲውል ሊወስን ይችላል።

## አንቀጽ 10
## የማኀበሩ የሥራ አመራር አካላት

ማኀበሩ ከዚህ የሚከተሉት የሥራ አመራር አካላት ይኖሩታል።

10.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

10.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ

10.3. ዋና ሥራ አስኪያጅ

10.4. ኦዲተር

## አንቀጽ 11
## ጠቅላላ ጉባዔ

11.1. የማኀበሩ ጠቅላላ ጉባኤየማህበሩ ከፍተኛ የስልጣን አካል ነው።

11.2. ጉባዔው መደበኛ ወይም አስቸኳይ ሊሆን ይችላል።

11.3. ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ የመመሥርቻ ጽሑፍ እና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሁሉ ባለአክሲዮኖችን በሙሉ ያስገድዳሉ።

11.4. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የማኀበሩ ሂሳብ ዓመት ከተፈፀመ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በየዓመቱ አንድ ጊዜ ይደረጋል።

11.5. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንደአስፈላጊነቱ ይደረጋል።

## አንቀጽ 12
## የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ

12.1. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳሬክተሮች ቦርድ ኦዲተሮች፣ ሂሳብ አጣሪዎች ወይም ፍርድ ቤት ናቸው። ጠቅላላ ጉባዔው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 366(2) እና 366(3) መሠረትም ሊጠራ ይችላል።

12.2. ጠቅላላ ጉባዔውን የሚመራው፣ የስብሰባ ቦታ፣ ጊዜና አጀንዳ የሚወስነው ስብሰባውን የጠራው አካል ነው። ቀደም ሲል በተደረገ ጠቅላላ ጉባዔ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ጉባዔው የሚደረገው የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ከተማ ነው።

12.3. የስብሰባ ጥሪ የሚደረገው ስብሰባ ከሚደረግበት ቀን ከ24 (ሃያ አራት) ቀን በፊት በጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ ወይም በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም በኢሜል እና አስተማማኝ በሆነ ሌላ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በሚጠራ ጥሪ አማካኝነት ይሆናል።

12.4. በመጀመሪያ ጥሪ ምልዓተ-ጉባዔ ካልተሟላ በድጋሚ ሌላ የስብሰባ ጥሪ የሚደረግበት ጊዜ በዕለቱ በተገኙት አባላት ይወሰናል። ሆኖም ከመጀመሪያው የስብሰባ ቀን በኋላ ለመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባዔ ከ24 (ሃያ አራት) ቀን የማያንስ ጊዜ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ደግሞ ከ8 (ስምንት) ቀን የማያንስ ጊዜ መስጠት አለበት። አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ለNስተኛ ጊዜም ሊጠራ ይችላል።

12.5. ማንኛውም ባለአሲዮን ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ በፊት ባለው አሥራ አምስት (15) ቀን ውስጥ ለጠቅላላ ጉባዔው የሚቀርበውን የሂሳብ ሚዛን ትርፍና ኪሣራ የዳይሬክተሮች ቦርድን እና የኦዲተሮች ሪፓርት እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ 381 እና 392 የተመለከቱ ሰነዶችን በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት በግንባር ቀርቦ ለመመልከት ወይም በራሱ ኪሳራ ግልባጭ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።

## አንቀጽ 13
## ስብሰባና ድምፅ የመስጠት መብት

13.1. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምፅ የመስጠት መብትን ይሰጣል።

13.2. የጉባዔው ድምፅ ቆጣሪዎች የሚመደቡትና የሚመረጡት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 380 በተመለከተው መሰረት ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው አባላት መካከል በሚደረግ ስምምነት ነው።

13.3. ማንኛውም ባለአክሲዮን ድምፅ የመስጠት መብት ይኖረው ዘንድ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 378 መሠረት በሚዘጋጀው መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት።

13.4. የባለአክሲዮን ወኪልነት ቅጽ በያዘ ወኪል አማካኝነት በጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ ለመስጠት ይቻላል። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን ከአንድ የበለጠ ወኪል መሾም አይችልም።

## አንቀጽ 14
## የመደበኛ የጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ አሰጣጥ እና ሥልጣንና ተግባር

14.1. በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያ ጥሪ ድምፅ የመስጠት መብት ከሚሰጡ የማህበሩ አክሲዮኖች ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶ (25%) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸውም ወይም ወኪሎቻቸው ካልተገኙ በቀር ጉባዔው ውሳኔ ለመስጠት አይችልም።

14.2. ምልዓተ-ጉባዔ ካልተገኘ ሁለተኛ ጊዜ የስብሰባ ጥሪ ይደረጋል። በሁለተኛው ጥሪ የተወከሉት ድምፅ የመስጠት መብት የሚሰጡ አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን፣ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል።

14.3. በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በድምፅ ብልጫ ነው።

14.4. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል።

14.4.1. ዳይሬክተሮችንና ኦዲተሮችን ይሾማል፣ የሥራ ዋጋቸውን ይወስናል።

14.4.2. የማኅበሩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሣራ እንዲሁም የዳይሬክተሮችን ሪፖርት ያፀድቃል፣ ይሽራል ወይም እንዲሻሻል ያደርጋል።

14.4.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያቀርበው ሐሳብ መሰረት የማኅበሩን የተጣራ ትርፍ ድልድል ይወስናል።

14.4.4. ማኅበሩ የግዴታ ወረቀቶችን (debentures) እንዲያወጣ ይፈቅዳል፤ከዚህ ጋር በተያያዘ ማኅበሩ የሚሰጠውን መያዣ ይወስናል።

14.4.5. በአንድ ጊዜ ወይም የመጀመሪያ ሽያጭ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከማኅበሩ ሀብት ውስጥ አምሳ አንድ በመቶ (51%) ወይም ከዚያ በላይ ማስተላለፍ የተፈለገ እንደሆን ይህንኑ ይፈቅዳል።

14.4.6. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 400 መሠረት በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን ሥር ከወደቁት ጉዳዮች በቀር በሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ውሳኔ ያሳልፋል።

14.4.7. የጠቅላላ ጉባዔው ውይይትና ውሳኔ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 387 በተመለከተው መሠረት በጽሑፍ በቃለ-ጉባዔ ተይዞ ቃለ ጉባዔውም በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮችና በፀሐፊው መፈረም አለበት።

## አንቀጽ 15

## አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ምልዓተ-ጉባዔ ድምፅ አሰጣጥ፣ ሥልጣንና ተግባር

15.1. ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 15.4 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ድምፅ የመስጠት መብት የሚሰጠው አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው ካልተገኙ በቀር ጉባዔው ውሳኔ ለመስጠት አይችልም። በመሆኑም ጉባዔው ውሳኔ ማሳለፍ የሚችለው

15.1.1. ለመጀመሪያ የጉባኤው ጥሪ አንድ ሶስተኛው (1/3)ያላነሰ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸውን አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

15.1.2. ለሁለተኛው የጉባኤ ጥሪ ከአንድ አራተኛ (1/4) ያላነሰ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸውን አክሲዮኖች የያዘ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ

15.1.3. ለNስተኛው የጉባኤ ጥሪ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብግምት ውስጥ ሳይገባ ባለአክሲዮኖች ወይም ወክሎቻቸው ሲገኙ

15.2. የማኅበሩ መመስርቻ ጽሑፍ ማሻሻል የማኅበሩን ዜግነት መለወጥ፣ ባለአክሲዮኖች በማኅበሩ ውስጥ ያላቸውን ማዋለ ነዋይ/ኢንቨስትመንት/ ከፍ እንዲደረግ ማድረግ፣ የማኅበሩን ካፒታል መቀነስ፣ መጨመር እና ማኅበሩን ማፈረስ የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው ሥልጣን ነው።

15.3. በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚተላለፍ ውሳኔዎች በተሰጠው ድምፅ በሁለት Nስተኛው (2/3 ኛ) መደገፍ አለባቸው።

15.4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 15.3 የተመለከተው ቢኖርም የማኅበሩን ዜግነት ለመለወጥና ባለአክሲዮኖች በማኅበሩ ውስጥ ያላቸውን መዋለ ንዋይ ከፍ እንዲያደርጉ የሚተላለፍ ውሳኔዎች እንዲሁም የማኅበሩን የንግድ ዓላማዎች ከትምህርት ሥራ ወደ ሌላ የንግድ ዓላማ ለመለወጥ የሚቻለው ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸውን አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በጉባዔው ላይ ተገኝተው በሙሉ ድምፅ ሲስማሙባቸው ብቻ ነው።

15.5. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው ውይይትና ውሣኔ በንግድ ሕግ አንቀጽ 387 በተመለከተው መሠረት በቃለ-ጉባዔ ተይዞ በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮችና በፀሐፊው መፈረም አለበት።

## አንቀጽ 16
## የዳይሬክተሮች ቦርድ

16.1. ማኅበሩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚሾሙ 9(ዘጠኝ) አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፣ የሥራ ዘመኑም 3(Nስት) ዓመት ይሆናል።

16.2. ማንኛውም ዳይሬክተር ሹመት ዘመኑ ሲያበቃ እንደገና ሊመረጥ ይችላል። የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ከ3 እስከ 13 ሊደርስ ይችላል።

16.3. የዲሬክተሮች ቦርድ ከአባሎቹ መካከል ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣል። ሊቀመንበሩም ሆነ ምክትል ሊቀመንበር በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ሊሻር ይችላል። ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር መሆን የሚችለው ባለአክሲዮን የሆነ ዳይሬክተር ነው።

16.4. ከዳይሬክተሮች ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ የበለጠ የቦርዱ አባል የጉደለ እንደሆነ በንግድ ሕግ አንቀጽ 303 መሰረት ይተካሉ።

16.5. ዳይሬክተሮች በስማቸው ከተመዘገቡ አክሲዮኖች 10(አስሩን) በዋስትና መልክ በማኅበሩ ዘንድ ያስቀምጣሉ። ስለሆነም የሥራ ዘመናቸውን ጨርሰው ኃላፊነታቸውን እስከሚያወርዱ ድረስ በዋስትና ያስያዟቸው አክሲዮኖቻቸው በሙሉ በማኅበሩ እጅ ይቀመጣሉ።

16.6. ዳይሬክተሮችን በሚመለከት ስለሚያዙ መዝገቦች የንግድ ሕጉ አንቀጽ 311 እና 313 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

16.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ የመመሥርቻ ጽሑፉን እና በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችን መሠረት በማድረግ የማኅበሩን ተግባራት ለመምራትና ለማስፈፀም የሚያስችል ሰፊ ሥልጣን ይኖረዋል።

16.8. በንግድ ሕጉ በአንቀጽ 269 እስከ 330 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው የዳይሬክተሮች ቦርድ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሥልጣን አሉት።

16.8.1. የማኅበሩ ዓላማ ግቡን እንዲምታ ሂደቱን በበላይነት ይቆጣጠራል ይጠብቃል፡፡

16.8.2. ዋና ሥራ አስኪያጁን እና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁን ይሾማል፣ ይቀጥራል፣ ደመወዝንና ሌሎች ጥቅሞቹን ይወስናል፣ ከሥራ ያስናብታል፡፡

16.8.3. ለዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑትን የሥራ ኃላፊዎች እና የማኅበሩን ፀሐፊ ሹመት ያፅድቃል፡፡

16.8.4. ጠቅላላ ጉባዔው የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች ተግባር ላይ ያውላል፣ ተግባር ላይ እንዲውሉም ያስደርጋል፡፡

16.8.5. የማኅበሩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያፀድቃል፡፡ የማኅበሩን ገንዘብ ሥራ ላይ ለማዋል እስትራቴጂና ፖሊሲዎችን ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

16.8.6. ማኅበሩ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚሸጥበትን ወይም በመያዥነት የሚሰጥበትን ስርዓት መመሪያ ያፀድቃል፡፡ ንብረት በመያዥነት ሲሰጥም ይህንኑ ያፀድቃል፡፡

16.8.7. የማኅበሩ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገዛበትንና የሚተዳደርበትን ሥርዓትና መመሪያ ያወጣል፡፡

16.8.8. የማኅበሩን የባንክ ሂሳብ የሚንቀሳቀስበትን ሥርዓትና መመሪያ ያወጣል ቼክ ፈረሚዎችንም ይሰይማል፡፡

16.8.9. የባንክ ብድሮችን ያፀድቃል፡፡

## <u>አንቀጽ 17</u>
## <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎች</u>

17.1. በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ የሚተላለፍ ውሳኔዎች የሚፀኑት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 308 እና 309 መሠረት የተላለፉ እንደሆነ ነው፡፡

17.2. በቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ በውክልና ስለመሳተፍ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 310 የተደነገገው ተፈፃሚነት ይሆናል፡፡

## <u>አንቀጽ 18</u>
## <u>ገደብ</u>

18.1. ማንኛውም ዳይሬክተር ከማኅበሩ ገንዘብ መበደር አይችልም፡፡

18.2. ማንኛውም ዳይሬክተር ማኅበሩን ዋስ ወይም ተያዥ ማድረግ አይችልም፡፡

18.3. ማንኛውም ዳይሬክተር በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ካልተፈቀደ በቀር ከማኅበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ካላቸው ወይም ሊኖራቸው በሚችሉ ድርጅቶች ውስጥ በኃላፊነት ሊሠራ አይችልም፡፡

## <u>አንቀጽ 19</u>
## <u>የዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

19.1. ዋና ሥራ አስኪያጅ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል

19.2. ዋና ሥራ አስኪያጅ

19.2.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን በተግባር ይተረጉማል

19.2.2. ከዳይሬክተሮች ቦርድ ቀጥሎ ለማኅበሩ አስተዳደር መካከል ያለው እሱ ነው፤

19.2.3. የማኅበሩን አስተዳደራዊ ፖሊሲዎች የማኅበሩን መዋቅርና የሰው ኃይል ዕቅድ የደመወዝ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም፣ በጀት እንዲሁም የመስፋፋት ዕቅዶችን እያዘጋጀ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ያቀርባል።

19.2.4. የማኅበሩ ፀሐፊ እና በቀጥታ ለራሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቦርዱን እያስፈቀደ ይቀጥራል፣ ደመወዛቸውንና ሌሎች ጥቅሞቻቸውን ይወስናል፣ ያሰናብታል።

19.2.5. ሌሎች ሠራተኞችን ይቀጥራል ደመወዛቸውን ሌሎች ጥቅሞቻቸውን ያስወስናል፣ ቦርዱን በማስፈቀድ ያስናብታል።

19.2.6. የማኅበሩን ገንዘብ ይሰበስባል፣ ማኅበሩ ሊከፍል የሚገባውን ዕዳ ይከፍላል።

19.2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድን በማስፈቀድ በማኅበሩ ስም ማናቸውንም የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ይፈርማል፣ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ሂሳቡንም የዳሬክተሮች ቦርድ ከሚሰይመው ሌላ የሥራ ኃላፊ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣ የባንክ ብድር ውልና ሌላ ማናቸውንም ውል ይዋዋላል፣ የማኅበሩን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ይሰጣል፣ በፍ/ቤት በNስተኛ ወገኖች ዘንድ ማኅበሩን ይወክላል።

19.2.8. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሕግ ጠበቃ ይሾማል፣ ይሽራል። ይህንኑ እንዲሁም ለማኅበሩ የሥራ ኃላፊ ወይም Nስተኛ ወገን በራሱ ሥላጣን የወክልና ሥልጣን ይሰጣል።

19.2.9. የዳይሬክተሮች ቦርድ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያቀርባቸውን የሀብትና ዕዳ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ አዘጋጅቶ ያቀርባል።

19.2.10. ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ክርክሮችን በዕርቅ ወይም በስምምነት ለመጨረስ ሥልጣን ይኖረዋል።

19.2.11. የዳሬክተሮች ቦርድ አባል ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም የቦርዱ ሊቀመንበር መሆን አይችልም።

## <u>አንቀጽ **20**</u>
## <u>የማኅበሩ ፀሐፊ</u>

20.1. ማኅበሩ አንድ ፀሐፊ ይኖረዋል፡ የፀሐፊው ቅጥርና ስንብት በሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በቦርዱ የሚፅድቅ ሲሆን ተጠርነቱ ለሥራ አስኪያጁ ይሆናል።

20.2. የማኅበሩ ፀሐፊ

20.2.1. የማኅበሩን መረጃዎችና መዛግብት ያደራጃል

20.2.2. ሪፖርቶችንና መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ይሰጣል ወይም ይልካል፣

20.2.3. ለባለአክሲዮኖችና ለNስተኛ ወገኖች መረጃ ይሰጣል፣

20.2.4. የባለአክሲዮኖችና የቦርድ ስብሰባዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ያደርጋል፣፣

20.2.5. የጠቅላላ ጉባዔዎችንና የቦርዱ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባዔዎች ይይዛል፣

20.2.6. በቦርዱ እና በሥራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 21
## ኦዲተሮች

21.1. የማኅበሩን ሂሳብ የሚቆጣጠር የውጭ ኦዲተሮች ይኖራሉ

21.2. ኦዲተሮች በጠቅላላ ጉባዔ ይሾማሉ፣ ይሻራሉ።

21.3. የሥራ ዋጋቸው በዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።

21.4. የኦዲተሮችን የሥራ ዘመን ሥልጣንና ኃላፊነት በሚመለከት በንግድ ሕግ በአንቀጽ 343 እስከ 354 የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 22
## የማኅበሩ ሂሳብ

22.1. በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ የዴሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን የንብረት ዝርዝር እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፤

22.2. የማኅበሩ የሂሳብ መግለጫዎችና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከሚደረግበት ቢያንስ ከአርባ ቀናት በፊት ለኦዲተሮች እና ለንግድ ሚኒስቴር መቅረብ አለባቸው።

## አንቀጽ 23
## የማኅበሩን ካፒታል ስለማሳደግ

23.1. አዲስ አክሲዮኖች በማውጣት ወይም ያሉትን አክሲዮኖች ዋጋ በመጨመር የማኅበሩን ካፒታል ማሳደግ ይቻላል።

23.2. የማኅበሩ ካፒታል የሚያድገው በንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 442 እስከ 460 በተደነገገው መሠረት በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ነው።

## አንቀጽ 24
## የሂሳብ ዓመት

የማኅበሩ የሂሳብ ዓመት ከሐምሌ 01 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል።

## አንቀጽ 25
## ስለ ማኅበሩ መፍረስ

25.1. ማኅበሩ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ከአንቀጽ 473 እስከ 491 በተደነገገው መሠረት ሊፈርስ ይችላል።

25.2. ማኅበሩ በሚፈርስበት ጊዜ ንብረቱ በሕግ በተደነገገው መሠረት ይጣራል።

## አንቀጽ 26
## ስለተሻሩ ደንቦች እና የመመሥርቻ ጽሑፍን ስለማሻሻል

26.1. በቀድሞ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር 823/40/92 በ10/06/92 እና በቁጥር 5799/8/95 በ4/9/1995 እንዲሁም በ24/1/2014 በቁጥር 12/2724/4ለ/2014 በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር ቀመ/7447/40/105 በ1/8/02005 የተረጋገጠና የተመዘገበ የመመሥርቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ማሻሻያዎች በሙሉ ተሽረው በዚህ የተሻሻለ እና የተጠቃለለ የመመሥረቻ ጽሑፍ ተተክተዋል።

26.2. ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በተደነገገው መሰረት በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሻል ይችላል።

## አንቀጽ 27
## ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

የባለአክሲዮን ስም፣ ዜግነት እና አድራሻ የሚያሳይ ሰንጠረዥ አባሪ 1(አንድ)

| ተ.ቁ | የባለአክሲዮን ሙሉ ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክልል/ከተማ | ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የቤት ቁጥር |
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| 4 | | | | | | |
| 5 | | | | | | |
| 6 | | | | | | |
| 7 | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | | | | | | |
| 9 | | | | | | |
| 10 | | | | | | |
| 11 | | | | | | |
| 12 | | | | | | |
| 13 | | | | | | |
| 14 | | | | | | |
| 15 | | | | | | |
| 16 | | | | | | |
| 17 | | | | | | |
| 18 | | | | | | |
| 19 | | | | | | |
| 20 | | | | | | |
| 21 | | | | | | |
| 22 | | | | | | |
| 23 | | | | | | |
| 24 | | | | | | |
| 26 | | | | | | |
| 27 | | | | | | |
| 28 | | | | | | |
| 29 | | | | | | |
| 30 | | | | | | |

የእያንዳንዱ ባለአክሲዩን ስም የያዘው የአክሲዮን ብዛት እና የከፈለው የአክሲዮን ዋጋ

ሰንጠረዥ አባሪ **2** (ሁለት)

| ተ.ቁ | የባለአክሲዮን ሙሉ ስም | የአንድ አክሲዮን ዋጋ | የአክሲዮን ብዛት | የተከፈለ ካፒታል መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | | | | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |
| 10 | | | | |
| 11 | | | | |
| 12 | | | | |
| 13 | | | | |
| 14 | | | | |
| 15 | | | | |
| 16 | | | | |
| 17 | | | | |
| 18 | | | | |
| 19 | | | | |
| 20 | | | | |
| 21 | | | | |
| 22 | | | | |
| 23 | | | | |
| 24 | | | | |
| 25 | | | | |
| 26 | | | | |
| 27 | | | | |
| 28 | | | | |
| 29 | | | | |
| 30 | | | | |